## በሥራ ሂደቱ ለሚሰጡ አገልግሎቶች የሚጠየቁ ቅድመ ሁኔታዎች

### የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማውጣት

#### ሀ/ ኢንቨስትመንቱ በግለሰብ በሚካሄድበት ጊዜ

- የኢንቨስትመንት ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ማቅረብ
- በባለሀብቱ /በህጋዊ ወኪሉ / የተሞላ የኢንቨስትመንት ማመልከቻ ቅጽ
- የኢንቨስትመንት ማመልከቻ ቅጽ በወኪል የተሞላ ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ
- የባለሀብቱ መታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ ወይም የሀገር ውስጥ ባለሀብትነት ሠርተፊኬት ፎቶ ኮፒ
- ሶስት የቅርብ ጊዜ ጉርድ ፎቶግራፍ

#### ለ/ የንግድ ማህበር በሚሆንበት ጊዜ

- የኢንቨስትመንት ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ማቅረብ
- የመመስረቻ ቃለ ጉባዔ
- በንግድ ማህበሩ /በወኪሉ/ የተሞላ የኢንቨስትመንት ማመልከቻ ቅጽ
- የማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶኮፒ፣ ማህበሩ አዲስ የሚቋቋም ከሆነ የማህበርተኞቹ የመታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ ወይም የሀገር ውስጥ ባለሀብትነት ሠርተፊኬት ፎቶ ኮፒ

#### ሐ/ የመንግሥት ልማት ድርጅት በሚሆንበት ጊዜ

- የኢንቨስትመንት ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ማቅረብ
- በልማት ድርጅቱ የበላይ ኃላፊ የተሞላ የኢንቨስትመንት ማመልከቻ ቅጽ፣
- የልማት ድርጅቱ የተቋቋመበት ደንብ ፎቶ ኮፒ ወይም የመመስረቻ ጽሑፍና የመተዳደሪያ ደንብ

#### መ/ የሕብረት ሥራ ማህበር በሚሆንበት ጊዜ

- የኢንቨስትመንት ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ማቅረብ
- በማህበሩ የበላይ ኃላፊ የተሞላ የኢንቨስትመንት ማመልከቻ ቅጽና የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ

#### ሠ/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በማስፋፋት ከሆነ /የማስፋፊያ ፈቃድ/

- የኢንቨስትመንት ኘሮጀክት ኘሮፖዛል ማቅረብ
- በማስፋፊያ ጠያቂው / ሕጋዊ/ ወኪሉ የተሞላ የማመልከቻ ቅጽ
- ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በንግድ ማህበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሐፍ እና የመተዳዳሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ
- የነባር ድርጅቱ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ

#### ረ/ የቡና ኢንዱስትሪ / ማጠቢያና ማበጠሪያ/ ከሆነ

- ከላይ በተራ ቁጥር ሀ እስከ ሠ ላይ ያሉት እንደተጠበቀ ሆኖ ከክልል ወይም ከዞን ገጠር ልማት መ/ቤት የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ

#### ሰ/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማደስ

- ዋናው የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሠርተፊኬት
- ጥያቄው የቀረበው በወኪል ከሆነ የውክልና ማመልከቻ
- ለዕድሳት የተዘጋጀውን ቅጽ መሙላት

#### ሸ/ የማበረታቻ ተጠቃሚ ለመሆን

♦ **የቀረጥ ነፃ ማበረታቻ**

- የኢንቨስትመንት ፈቃድ ያወጣና ያደሰ እንዲሁም ማበረታቻ በሚሠጥባቸው የሥራ መስኮች የተሠማራ፣ኮሜርሺያል ኢንቮይስ ወይም ኘሮፎርማ፣ ካታሎግ እንደአስፈላጊነቱ፣ የውጪ ምንዛሪ ፈቃድ እና የማስጫኛ ሠነድ ማቅረብ።

♦ **የገቢ ግብር ማበረታቻ**

- የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቱ ግንባታውን አጠናቆ የሥራ ፈቃድ ያወጣ መሆን

♦ **የመሬት ክራይ እፎይታ**

- በባለሀብቱ ወይም በወኪሉ የቀረበ ማመልከቻ
- የአፈፃፀም ሪፖርት
- የኢንቨስትመንት ኘሮጀክቱ ግንባታውን አጠናቆ የሥራ ፈቃድ ያወጣ መሆን

#### ቀ/ ከኢንቨስትመንት ፈቃድ ጋር በተያያዙ የሚቀርቡ የለውጥ ምትክና ስረዛ ጥያቄዎችን በተመለከተ

♦ **የስም ዝውውር ከግለሰብ ወደ ማህበር ለማስደረግ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች**

- ማመልከቻ፣ የማሻሻያ ወይም የለውጡ መመስረቻ ጽሁፍና የፀደቀ መተዳደሪያ ደንብ ፣ የዋና ምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ካርድ፣ ማመልከቻ በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ስልጣን ማረጋገጫ፣ ውሉ ውል ለመመዝገብ በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ስለመመዝገቡ የቀረበ ማረጋገጫ።

#### በ/ በሽያጭ ወይም በስጦታ ከሆነ

- ማመልከቻ፣ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽህፈት ቤት የፀደቀ የሽያጭ ወይም የስጦታ ስምምነት ማስረጃ፣ የዋና ምዝገባ ምስክር ወረቀት ፣ የኢንቨስትመንት ሠርተፍኬት፣ የግዥ ወይም የስጦታ ተቀባይ የቅርብ ጊዜ ጉርድ ፎቶ ግራፍ፣ የግብርና ኘሮጀክት ከሆነ ኘሮጀክቱ በመልማት ላይ ያለ መሆን፣ በፈቃዱ ስም ብድር የወሰደና በመስሪያ ቤቱ ደረጃ የተመዘገበ ከሆነ ያበዳሪ ክፍል አስተያየት እና በወኪል የቀረበ ከሆነ የውክልና ማረጋገጫ

#### ተ/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማሰረዝ

- ለመሠረዝ ያስፈለገበትን ምክንያት ያዘለ ማመልከቻ፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ሠርተፍኬት፣ የምዝገባ ምስክር ወረቀት፣ በኢንቨስትመንት ፈቃድ የተገኙ ጥቅማ ጥቅሞችና የተገቡ ግዴታዎችን በደንቡ መሠረት የተወጣ መሆኑን ማረጋገጫ፣

#### ቸ/ የኢንቨስትመንት መሬት ለማግኘት

#### የገጠር ኢንቨስትመንት መሬት ለማግኘት

- ማንኛውም ባለሀብት በገጠር ለሚያካሂደው የኢንቨስትመንት ሥራ መሬት ለማግኘት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ከኘሮጀቱ ካፒታል ቢያንስ 35 በመቶው በባንክ ሂሳብ እንዳለ የሚያሳይ ማስረጃ ካቀረበ በኃላ ከሚከተሉት ሠነዶች ጋር ለሥራ ሂደቱ ያቀርባል፣ ለኘሮጀክቱ የሚውል የመሬት መጠን ይወስናል፣ የመሬት ውል ከመፈፀሙ በፊት የግማሽ አመት 50% ቅድሚያ የመሬት ኪራይ ተመን ክፍያ ያስከፍላል፣ ባለሀብቱ የመሬት ኪራይ ውል እንዲፈጽም ያደርጋል፣ መሬቱን በመለካት ካርታና ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት በማዘጋጀት መሬቱን ያስረክባል።

# የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ የሥራ ሂደት

# አገልግሎት አሰጣጥ

## ኢንቨስትመንት ማስፋፊያ የሥራ ሂደት ሥልጣንና ተግባር

- በክልሉ የኢንቨስትመንት ሀብት ሥራ ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ያስፋፋል፣
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ ይሰጣል፣ ያድሳል፣ ያግዳል፣ ይሠርዛል፣
- ምቹ የኢንቨስትመንት ሁኔታዎችን ለመፍጠር የሚያስችል የፖሊሲና የአፈጻጸም ሀሳቦችን ያመነጫል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
- ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ለማስፋፋት የሚረዱ ጥናቶችንና ሥልጠናዎችን ያዘጋጃል፣
- ለባለሀብቶች ቅድመና ድሕረ ኢንቨስትመንት የድጋፍና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣
- ለኢንቨስትመንት የተከለሉ ቦታዎችን ከሚመለከተው አካል ተረክቦ ለኢንቨስትመንት እንዲውል ያደርጋል፣
- የክልሉን የሀብት ክምችት መረጃ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች በመሰብሰብ የኢንቨስትመንት ኘሮፋይል ያዘጋጃል፣ ያሰራጫል፣
- ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚረዱ ሕትመቶችን፣ ዶክመንተሪ ፊልሞችንና የመሳሰሉትን አዘጋጅቶ ያሰራጫል፣
- የኢንቨስትመንት ፈቃድ የተሰጣቸውን ኘሮጀክቶች ይከታተላል፣ ባለሀብቶች ግዴታቸውን መወጣታቸውን ያረጋግጣል፣
- የተለያዩ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል፣ እንደአስፈላጊነቱ አዳዲስ ማበረታቻዎችን እያጠና ለሚመለከተው አካል ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
- ለባለሀብቶች የተሰጠና የተዘጋጀ የገጠር መሬት እንዲለካና የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተዘጋጅቶ እንዲሰጥ ያደርጋል፣
- ከወጪ ምርት ጋር የተገናኙ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎችን ያበረታታል፣ ለባለሀብቶች የቴክኒክና የምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

**ስልክ** 046 220 33 00
046 221 03 67
046 221 03 68
046 221 03 69
**ፖስታ** 328
**ፋክስ** 046 220 32 65
E-Mail:snnpinv@ethionet.et
www. southinvest.gov.et
Awassa-Ethiopia

# የሥራ ሂደቱ ራዕይና ተልዕኮ

## ራዕይ

ክልሉ በኢትዮጵያ ግንባር ቀደም የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የሚካሄድበት ቦታ ማድረግ የሚችል ጠንካራ የአንድ ማዕከል ተቋም ሆኖ ማየት::

## ተልዕኮ

የክልሉን ሕዝብ ኑሮ ደረጃ ለማሻሻል በክልሉ ያለውን ሰፊ የተፈጥሮ ሀብትንና የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማጥናትና በማስተዋወቅ፣ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመስጠት፣ ባለሀብቶችን በማበረታታትና መሬት የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት፣ አፈጻጸማቸውንም በመከታተልና የሚከሰቱ ችግሮችን በተለያዩ አቀራረቦች በማቃለል ክልሉን ለኢንቨስትመንት ምቹ ማድረግ ነው::

## እሴቶች

- የመንግስት ፖሊሲና ስትራቴጂ የዕቅዶቻችን መርሆዎች ናቸው፣
- ፍትሐዊ አሳታፊና ዴሞክራሲያዊ አመራር መለያችን ነው፣
- የሰው ሀይል ካሉን ሀብቶች ሁሉ ቀዳሚ ሀብታችን ነው፣
- ሥራዎቻችን የጋራ አመለካከትና ግንዛቤ ከመፍጠር ይጀምራሉ፣
- የአገልግሎቶቻችን ተጠቃሚዎችን እናከብራቸዋለን ደመወዛችንን የሚከፍሉን እነሱ ናቸው::
- ቅሬታ አቅራቢዎች መካሪዎቻችን ናቸው፣
- ቀጠሮ ማክበርና ማስከበር ባህላችን እናደርገዋለን::
- ጥራት፣ ግልፀኝነት፣ ተጠያቂነት፣ ፍጥነት እና ታማኝነት አምስቱ ጥምር የስራ ሂደታችን ሀብቶች እናደርጋቸዋለን::
- ሁሌም ተማሪና አስተማሪ ነን
- አለቃችን ሥራችን ነው ሥራውም ውጤቱም የኛ ነው::

## የሥራ ሂደቱ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች

ሀ/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት ፣

ለ/ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማደስ፣

ሐ/ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት የወጡ የተለያዩ ማበረታቻዎችን መፍቀድ

መ/ ከኢንቨስትመንት ፈቃድ ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ የለውጥ፣ ምትክ መስጠትና ስረዛ ማካሄድ

ሠ/ የመረጃና የምክር አገልግሎት መስጠት

ረ/ የፕሮጀክት ፕሮፋይል ማዘጋጀት ፣

ሰ/ ለአልሚ ባለብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የሚያስፈልግ መሬት በመለካት ከይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ጋር ማስረከብ፣

ሸ/ ለባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ድጋፋዊ ክትትል በማድረግ የመረጃ፣ የምክርና የሥልጠና አገልግሎት መስጠት እና ለሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሐ መስጠት

| ተ.ቁ | የአገልግሎት አይነት | የአሠራር ቅደም ተከተሉ የሚያልፍባቸው ሂደቶች ብዛት | አገልግሎቱን ለመፈጸም የሚወስደው ጊዜ (በደቂቃ) |
|---|---|---|---|
| 1 | የባለሀብት ፕሮጀክት ፕሮፖዛል ግምገማ | 1 | 1 ቀን /450 ደቂቃ/ |
| 2 | ቅድመ ሁኔታዎችችን አሟልቶ ላቀረበ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት | 5 | 20 |
| 3 | የኢንቨስትመንት ፈቃድ እድሣት | 3 | 20 |
| 4 | የኢንቨስትመንት ማበረታቻ ለማግኘት | 1 | 15 |
| 5 | የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለውጥ፣ ምትክ ፣ስረዛ | 3 | 20 |



| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነትና የክፍያ ምክንያቶች | የአገልግሎት ክፍያ ዋጋ /በብር/ |
|---|---|---|
| 1 | አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት | 600 |
| 2 | የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማደስ | 200 |
| 3 | የማስፋፊያ ኢንቨስትመንት ሠርተፊኬት | 300 |
| 4 | የማስፋፊያ ኢንቨስትመንት ለማደስ | 100 |
| 5 | ለኢንቨስትመንት ማመልከቻ ቅጽ | በነፃ |
| 8 | ምትክ የኢንቨስትመንት ፈቃድ / የምስክር ወረቀት መስጠት/ | 100 |
| 9 | ለኢንቨስተሮች መረጃ መስጠት | በነፃ |

“ኤድስን በጋራ እንከላከል”